# ቀስተደመና ሬድዮ ትችት

(12.07.02)

# «የአፍሪካ ህብረት» አዲስ ወይስ አጓጉል ጅማሮ?

በ1955 አዲስ አበባ ከተማ ተመስርቶ የነበረው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፈርሶ ያለፈው ረቡ ሃምሌ ሶስት ቀን 1994 አ.ም. በደቡብ አፍሪካ ደርባን ከተማ የአፍሪካ ህብረት የተባለ አዲስ አህጉ ራዊ ድርጅት ተቋቁሟል። የምስረታው ስነስርአት በተለመደው የመሪዎች «የእንኳን ደስ ያለን» ዲስ ኩሮች፣ በርችትና በባህላዊ ድለቃ ታጅቦ የተጠናቀቀውን ያህል ህብረት ተፈጠረላችሁ በተባሉት በአ ፍሪካ ህዝቦች ዘንድ ግን እንኳን ጭፈራና ድለቃ ቀርቶ ስለዚህ ታሪካዊ የተባለ ክስተት ቅንጣት ግን ዛቤ ያለ አይመስልም።

ከዚህ ለአፍሪካ አህጉራችን አዲስ ጅማሮ እየተባለ ከሚነገርለት ህብረት ምስረታ ምን አዲስ ነ ገር መጠበቅ ይቻላል? ይህንን ለመመለስ መጀመሪያውኑ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ለም ን ተመስርቶ ምን ሰራ? ምን አልሰራም? ለምን? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል። ሁለቱ የ ተቋቋሙባቸው ወቅቶች እንደሰማይና ምድር የተለያዩ ወቅቶች ናቸው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም ወቅቱ ከኬንያና አንጎላ ጀምሮ ወደ ደቡብ ያለው የአህጉ ሩ ክፍል ገና በቅኝ ግዛት የተያዘበት፤ ደቡብ አፍሪካ ደግሞ በአፓርታይድ አገዛዝ የተያዘችበት ወቅ ት ነበር። እርግጥ በእነአጼ ሃይለስላሴ፣ኩዋሜ ኑክሩማ፣ ገማል አብደል ናስር፣ ሴኩ ቱሬና ሌሎች ም «ካዛብላንካ ቡድን» ተብለው ይታወቁ በነበሩት ዙሪያ ቅኝ አገዛዝን ካህጉሩ አስወግደን ባጭር ጊ ዜ ወደ አንድነት መሄድ አለብን የሚል ስር ነቀል አስተሳሰብ ነበር። ይህንን በመቃወም ደግሞ በነ ሊዮፖልድ ሴንጎር፤ ሁፍዌት ቡዋኝ ወዘተ የሚመራው «የሞንሮቭያ ቡድን» ደግሞ መጀመሪያ የአፍ ሪካ አገሮች በሙሉ ከቅኝ ግዛት የሚላቀቁበት ትግል የሚያከሂድ፤ እያንዳንዱ ነጻ የአፍሪካ አገር መ ጀመሪያ የየራሱን የአገር ግንባታ ከግብ የሚያደርስበት አካሄድ መቅደም አለበት ሲል ተከራከሯል።የ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት በአሸናፊነት የወጣው ይህ ሁለተኛው አቋም ነበር። በመሆኑም ይህ ድርጅት ምንም እንኳን በረጅም ጊዜ አፍሪካ ወደ አንድነት የምትሄድበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚል አላማ ቢኖረውም ባጭር ጊዜ ግን ትኩረቱ ቅኝ ግዛትንና አፓርታይድን በጋራ መታገል ከዚያ በተረፈ ግን ድርጅቱም ሆነ ማንም አባል አገር በሌላ አባል አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክል አሰራር ነበረው።

ቅኝ ግዛትንና አፓርታይድን በመታገልና በማስወገድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የማይናቅ ሚና ተጫውቱዋል። በዚህ በኩል ተልእኮውን ተወጥቷል ማለት ይቻላል። በአፍሪካ ሰላምን የማስፈን፣ ል ማትን የማምጣት፣ ዴሞክራሲን የማረጋገጥ አላማዎች እስከዚህም የሚተኮርባቸው ነጥቦች አልነበሩ ም። አልተተኮረባቸውም። አገሮች ለጠቅላላ ለአህጉሩ አሳፋሪ ሊባሉ የሚችሉ እንደ ኢዲ አሚንና ካስር አለቃነት ወደ ንጉሰ ነገስትነት እንደተሽጋገረው ቦካሳ አይነት ወንበዴዎች ስር ሲወድቁ በአባል መንግስታት ጉዳይ ጣልቃ መግባት አይችልም የተባለለት አእድ ምንም ማድረግ አልቻለም። በሰላ ሙም፣ በልማቱም መስክ የሆነ ነገር ለመስራት ተልእኮውም ሆነ አቅሙና መዋቅሩ ስለማይፈቅድለት ይህ ድርጅት ከቅኝ ግዛትና ካፓርታይድ መወገድ በኋላ እየከሰመ እየተልፈሰፈሰ ስራ የፈታ ተቋዋ ም እየመሰለ መሄዱ ምንም ሊያስገርም አይችልም።

በመሃል አፍሪካ በኢኮኖሚ እድገት ጎዳና እየደቀቀች፤ ማህበራዊ ፍትህ ደብዛው እየጠፋ፣ ህዝ ቦቿ ካመት አመት እየደኸዩ የሚሄዱበት አስከፊ አቅጣጫ ተያዘ። ህዝቦች በመንግስቶቻቸው እምነ ት እያጡ፣ መንግስታት ስለህዝቦች ያላቸው ግድየለሽነት እየጨመረ መጣ።። የዛሬ አርባ አመት ቀ ርቶ አህጉራችን በታሪኳ አይታ በማታቀው ሁኔታ የትርምስ፣ ያለመረጋጋት፣ የበሽታ፣ የርሃብ፣ የመከ ራ አህጉር ሆነች።

የአይድሱ መቅሰፍት፣ የርሃቡን ችግር፣ የአካባቢ ውድመት በሚፈጥራቸው የማህበራዊና የኢኮ ኖሚ ቀውሶች ላይ እንዲያውም በነሱ እየታገዘና እነሱን መልሶ የሚያባብስ የሰላም መጥፋት አህጉሪ ቱን ወደ ጥፋት አዝቅት ይዞ የሚነጉድ የአጠቃላይ ቀውስ ወቅት ውስጥ ገባን። ቀዝቃዛወዘ ጦርነት አከተመ ከተባለ ወዲህ ግጭቶች በአህጉራችን እየተባባሱ በመምጣታቸው ባለፉት አስር አመታት በ

ጦርነትና ከጦርነት በተያያዙ ምክንያቶች ህይወታቸውን ያጡ አፍሪካውያን ቁጥር አራት ሚልዮን ይገመታል። ዛሬ በመሃከላዊ አፍሪካ ሩዋንዳ፣ ዩጋንዳ፣ ዚምባብዌ፣ አንጎላና ዴሞክራቲክ ኮንጎ የሚራኮቱበት አውዳሚ ጦርነት፤ በቡሩንዲ በኮንጎ ብራዛና በሱዳን የሚካሄደው የእርስ በርስ ትርምስ፣ በምእራብ አፍሪካ በጊኔ፣ ላይቤርያና ሴራ ልዮን አዋሳኝ የምካሄደው አረመኔያዊ ጦርነት በሱማሊያ ላለፉት አስር አመታት የቀጠለው ትርምስ፣ በኢትዮጵያና ኤርትራ መሃከል የተካሄደውና እንደገና ሊያገረሽ ይችላል ብለን የምንሰጋው ጦርነት አህጉራችን ትልቅ ቀውስ ውስጥ መሆኗንና ህልውናዋን ካልን አንድ መፍትሄ መሻት እንዳለብን የሚጠቁም ቀውስ ነው።

ጥያቄው እንግዲህ አዲሱ ህብረት ለዚህ መፍትሄ ለመሻት የሚሰራ ህብረት ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። በኛ በኩል ያለው መለስ አጭር ነው። መሪዎቹ የአፍሪካ ችግር ገብቷቸው አዲስ ጅማሮ ብለው ተነስተዋል። ለዚህ ችግር የሚሰጡት መልስ ግን አጉዋጉል መልስ ነው።

ዛሬ የአፍሪካ ዋናው ችግር እየከፋ የሚሄደው የህዝቦቿ መደህየትና ይህ ድህነት እየፈለፈላችው ያሉት ጦርነቶች መልሰው ድህነትን ማጣትንና መራቆትን እያስፋፉ አስከፊ የሆነ የጥፋት አዙሪት ውስጥ መውደቋ ነው። ኮፊ አናን በምስረታው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር በአህጉራችን ጦርነቶች ካልቆሙና መረጋጋት ካልተገኘ ምንም አይነት የልማት እርዳታ ቢመጣ ችግራችን አይፈታም በማለት የሰላምን ቁልፍ ጥያቄነት አስምረውበታል። የህብረቱ መስራች መሪዎችም የአፍሪካ የወደፊት እድል ሊሰምር የሚችለው ሰላም፣ ዴሞክራሲ፤ የህግ የበላይነት፣ መልካም አስተዳደር እና ልማት ተጋግዘው የሚሰፍኑበት ሁኔታ ሲመቻች ብቻ እንደሆነ በማመን የአፍሪካ ህብረት እነዚህ ተግባራት ላይ እንዲያተኩር አስፈላጊ የሆነው ተልእኮና አወቃቀር እንዲኖረው አድርገዋል።

በሃገሮች መሃከል ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እንደዚሁም የሃገሮች የውስጥ ጉዳይ ነው እየተባለ እንደሩዋንዳ የጅምላ ግድያ እንዳይከሰት የአፍሪካ ጸጥታ ምክር ቤትና አፍሪካዊ የጸጥታ አስከባሪ ሃይል ይኖራል ተብሉዋል። ቀስ በቀስ አንድ የአፍሩካ ማከላዊ ባንክ፣ የአፍሪካ ፓርላሜንት፣ የአፍሪካ መአከላዊ ፍርድ ቤት ይቋዋቋዋማሉ ተብሉዋል። ሰብአዊ መብቶችንና የህግ የበላይነትን እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ «በአቻዎች መሃከል ግምገማ» (ፒር ሬቪው) የሚካሄድበት አሰራርምየኖራል ተብሉዋል። ይህ ሁሉ ባልከፋ ነበር።

ቁልፉ ጥያቄና ቁልፉ ቀውስ ድህነትና ትርምስ ናቸው ብለናል። በተለይ ከአስር አመታት ወዲህ በነዚህ በሁለት መቅሰፍቶች መሃከል ያለው ግንኙነት ሶስት ገጽታዎች አሉት።

በአንድ በኩል ለበለጸጉት አገሮች ብቻ በተመቻቸ ሁኔታ እየተበጀ ባለው የግሎባላይዜሽን ስርአት አህጉራችን ለይበልጥ ድህነት እንጂ ለልማት በማይመች ሁኔታ ዘው ብላ በመግባቷ ምንም እንኳን ለጥቂት የየሃገሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አፍታ ሃይሎች (ኤሊትስ) የመክበር አጋጣሚ ቢያመጣም የአፍሪካ ህዝቦች እየጨመረ ለሚሄድ ድህነት እየተጋለጡ ናቸው።

ሁለተኛው ገጽታ ይህ ዛሬ በአለም ላይ እየተተከለ ያለው ግፈኛ የግሎባላይዜሽን ስርአት ካመት አመት አህጉሪቱን የባሰ ቀውስ ውስጥ እየጨመረ መሄዱ አይን ላለው ሁሉ የሚታይ ክስተት ሆኖ ሳለ በመንግስት ደረጃም ሆነ በተቃዋሚነት ጎራ ያሉት የፖለቲካ መሪዎች በጥቅምም ይሁን በርእዮተ አለም ምርጫ፣ በታክቲክም ይሁን የማይበገር ለሚመስለው ሂደት ተስፋ ቆርጠው በመንበርከክለዚህ ለነጻና ስድ ገበያ ስርአት አማራጭ አያቀርቡም።

ግሎባላይዜሽን፣ እየጨመረ የሚሄድ ድህነትና የፖለቲካ መሪዎች የአማራጭ ክስረት ሲደማመሩ ደግሞ ሶስተኛውን ገጽታ ያስከትላሉ። ሩቅ ሳንሄድ በኛ አገር እንኳን በግልጽ እንደምናየው ከነጋዴው፣ ከሃገራዊ አምራቹ፣ ከሰራተኛው በስተቀር በግሎባላይዜሽን ክልል ውስጥ ለመደላደል የሚከጅለውን የነጻ ገበያውን ኢኮኖሚ ከጥያቄ ውስጥ የሚያገባ የፖለቲካ ሃይል የለም። ቀውሶቹ የሚፈጥሩዋቸው ህዝባዊ ትግሎች አህየአውን ፈርቶ ዳውላውን እንዲሉ ዋናው ጣላት መሳሪያ እያቀበለ ወንድም በወንድሙ፣ ድሃ በድሃ ላይ የሚዘምትባቸው «እጅ አግር የሌላቸው» ትርምሶች መልክ ይይዛሉ። በፖለቲካ መሪዎች መሃከል በሚደረገው የስልጣን፣ የኢኮኖሚ ጥቅም ሽኩቻ ድሃው ህዝብ በጎሳ፣ በሃይማኖት፤ ባካባቢ ጎራ እየለየ እንዲታገልና እንዲሰዋ ይደረጋል።

የአፍሪካ ህብረት መስራቾች ይህ «የአማራጭ ቀውስ» አለ ብለው የሚጠረጥሩ እንኩዋን አይመስሉም። ድህነትና ሰላም መጥፋት የተያያዙ መሆናቸውን ቢገነዘቡም ድህነትን በዚህ ለሁሉም እኩል እንዲሰራ ሆኖ ባልተመቻቸ አለም አቀፍ ስርአት ውስጥ ይበልጥ በመዋሃድ አሸንፈን ባህጉራችን ሰላምና ልማትን እናሰፍናለን የሚል አደገኛ ቅዠት ውስጥ ያሉ ይመስላሉ። ለዚህም የህብረቱ የኢ

ኮኖሚ እድገት የተቀየሰበት ኔፓድ ወይም «አዲስ ትብብር ለአፍሪካ እድገት» የሚል ሰነድ አጽድቀ ዋል።

ሰነዱ የአፍሪካ ዋና ችግር ከአለም ኢኮኖሚ መገለሉዋ ነው ብሎ ስለሚነሳ እድገቱዋን ለማፋጠ ን በይበልጥና በፍጥነት አለም ኢኮኖሚ ውስጥ መዋሃድ አለባት የሚል እምነት ላይ የተገነባ ሰነድነ ው።

ስለምን «ከአለም ኢኮኖሚ መገለል» ነው የሚወራው? አፍሪካ የተገለለችው ከአለም ኢኮኖሚ ሳይሆን ይህ ኢኮኖሚ ከሚሰጠው ጥቅም ነው። ሰላሳ ሚልዮን አፍሪካውያን በባርነት ተፈንግለው ከ ምድራቸው ሲፈናቀሉ ትኩስ አምራች ሃይሉዋን ያከሰመው የባሪያ ፍንገላ ስርአት ከአለም ኢኮኖሚየ መዋሃድ ሂደት ነበር። በተከተለው የቅኝ አገዛዝ ዘመን እየተዛቀ የተወሰደው ማእድኑዋና ሌላ የተፈ ጥሮ ሃብት፣ ዛሬ የአፍሪካ ህዝቦች ጥረው ግረው ያስተማሩዋቸውን ምሁራን እያሙዋጠጠ ወደ ሰሜ ን አገሮች የሚወስደው የእውቀት መፍለስ (ብሬይን ድሬይን) ይህ ሁሉ የአፍሪካን ካለም ኢኮኖሚ መገለል አያሳይም። የሚያሳየው በአጉዋጉል፣ ባልመረጠችውና በማያመቻት ሁኔታ በአለም ኢኮኖሚ ውስጥ መዋሃዱዋንና መዳከሩዋን ነው። ኔፓድ ለመቀጠል የሚፈልገው በዚህ አቅጣጫ ነው።

የኔፓድ ሌላው የእድገት ተብየ አቅጣጫ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ኤክስፖርት ላይ አተኩሮ ከ ዚያ በሚገኘው የውጭ ምንዛሪ የአፍሪካን እድገት ማፋጠን የሚል ነው። እንዲያውም የኔፓድ አርቃ ቂዎች አንዱ መሰረታዊ ጥያቄያቸው ኤክስፖርት ላይ አተኩረን እንድናድግ የበለጸጉት አገሮች ለኛ ምርቶች ገበያቸውን መክፈት አለባቸው የሚል ጥያቄ ነው። ይህም ማንንም እንዳላስኬደ አፍሪካንም አያስኬድም። ዛሬ አድገዋል ለምተዋል ከሚባሉት ታላላቅ አገሮች የማናቸውም ኢኮኖሚ በኤክስፖ ርት ላይ አተኩሮ አላደገም። ከሃገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ሲነጻጸር ባጠቃላይ በሃያኛው ክፍለ ዘመ ን የበለጸጉት አገሮች ከምርታቸው የኤክስፖርት ድርሻ ካስራ አምስት ከመቶ አልፎ አያውቅም። አ ፍሪካ ግን ዘይቱም፣ ማእድኑም፣ ቡናውም ሌላ የተፈጥሮ ሃብቱም ሲደማመር ህዝቦቹዋ ምንም አይ ጠቀሙበትም እንጂ ከጠቅላላ ምርቱዋ ካርባ እስካርባ አምስት ከመቶ ኤክስፖርት ታደርጋለች። ይህ ስትራቴጂ እስካሁን ለህዝቦቹዋ ምንም ያስገኘው ነገር የለም።

ኔፓድ ባለም ደረጃ የንግድ ልውውጥ ቢጧጧፍ አፍሪካ በአጭር ጊዜ የማደግ ተስፋ አላት ብ ሎ ያምናል። ነገር ግን ደግሞ ነጻ ገበያ ይባል እንጂ ዛሬ ያለው የአለም አቀፍ የንግድ ህግ የበለጸጉ ት አገሮች ሲመቻቸው የሚያከብሩት ሳይመቻቸው ደግሞ ደብዛውን የሚያጠፉት አሰራር ነው። በነ ጻ ገበያ አሰራር መሰረት ታሪፍ ዝቅ አርጉና ሸቀጣችንን እያራገፍን የእናንተን ታዳጊ ኢንዱስትሪዎች እናክስም በሚሉበት አፋቸው የአፍሪካ ምርቶች እነሱ አገር እንዳይገቡ ታሪፍ እንቆልል ይላሉ። የአ ፍሪካ ህዝብ በርሃብ እየተቆላ ገበሬው አምርቶ ሃገሮች በምግብ ራሳቸውን እንዳይችሉ አሁንም ከነጻ ገበያ አሰራር ውጭ ለራሳቸው ገበሬ ድጎማ እያደረጉ በአልባሌ ዋጋ አፍሪካ ላይ እህል፣ ወተት፤ ስጋ በማፍሰስ ድሃውን አምራች ከገበያ እንዲወጣ ያደርጋሉ።

ኔፓድ በአጭሩ የኢኮኖሚ እድገትንና የሃገር ልማትን የሚያምታታ ከስራ ላይ ቢውል እርግጥ ጥቂቶችን አክብሮ ብዙሃኑን ግን ለባሰ ድህነት የሚዳርግ እቅድ ነው። በዚህ ሰነድ ላይ ተመርኩዞ ያፍሪካን እድገት ማረጋገጥ አይቻልም። በመሆኑም አዲሱ ያፍሪካ ህብረት ዋና አላማየ ብሎ የተነሳ በት ሰላምና ልማት በዚህ ሰነድ አማካኝነት አይሳካም። ሰላምና መረጋጋት፣ እድገትና ልማት የሚረጋ ገጡት እዚህ አደገኛና ግፈኛ አለም አቀፋዊ ስርአት ውስጥ ዘው ብሎ በመግባት ሳይሆን ለአፍሪካ ህዝብ እድገት አፍሪካዊ ራእይ ያለው ሌላ አማራጭ ስንይዝ ብቻ ነው።

የዛሬ አርባ አመት በፊት የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ነጻ እየወጡ እንደዚሁ እንደዛሬው ከህ ዝቦቻቸው ህልምና ፍላጎቶች ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው የእድገት እቅዶች ሲነደፉ የታዘበ አን ድ ረኔ ዱሞ የተባለ ደራሲ «ፎልስ ስታርት ኢን አፍሪካ» ማለትም «አጉል አጀማመር በአፍሪካ»በ ሚል ርእስ የጻፈውን ታሪካዊ ራእይ ያለው ማስጠንቀቂያ መጽሃፍ የሚያስታውሱ ብዙ አፍሪካውያን ምሁራን ኔፓድ የተባለው እቅድ ይፋ ከሆነ ወዲህ ይህንኑ ማስጠንቀቂያ እየደገሙ ናቸው።

የአፍሪካ ህብረት የተባለው ድርጅት በዚህ ሰነድ ተመርቼ ለአፍሪካ ሰላምንና ብልጽግናን አመጣ ለሁ የሚል ከሆነ እኛም አጀማመሩ አጉል አጀማመር ይሆናል የሚል ተጨባጭ ስጋት አለን።